የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሣያ ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.78
Addis Ababa 28th day of Jun, 2024


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፲፮

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ማሻሻያ ደንብ

ገፅ.......................................................፫ሺ፬፻፴፱


**CONTENTS**


Regulation Number 168/2024

The Addis Ababa City Government Strategic Programs Management Office Establishment Amendment Regulation

Page ............................................ 3439


**ደንብ ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፵፯/፪ሺ፲፭ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን እንደገና በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፺፬ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ (ማሻሻያ) ቁጥር ፻፷፰/፪ሺ፲፮/» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**Regulation Number 168/2024**

**A Regulation to Provide for the Amendment of regulation No. 147/2023 issued for the for the Establishment of the Addis Ababa City Government Strategic Programs Management Office**

**WHEREAS,** it has been found necessary that to improve the power and duties of the Addis Ababa City Government Strategic Programs Management Office;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as: "Amendment for Regulation No. 147/2023 issued for the Establishment of the Addis Ababa City Government Strategic Programs Management Office Regulation No. 168/2024."

**፪. <u>ትርጉም</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ፻፵፯/፪ሺ፲፭ነው፤

፪. በደንቡ ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፫. <u>ማሻሻያ</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስትራቴጂክ ፕሮግራሞች ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፵፯/፪ሺ፲፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩. ከደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮)፣ (፯) እና (፰) ተጨምረዋል፣

«፮. ለሬዚሊየንት ስትራቴጂ ትግበራ ከተለያዩ የሀገር ውስጥ፣ ክልል እና የውጭ ሀገር የግል ዘርፍ አካላት ጋር አጋርነትን ይመሰርታል፤

፯. ለሁሉም ዘርፎች የሬዚሊየንስ ስትራቴጂ ለማስፈጸም አዋጭ ፕሮጀክቶችን ያሰናዳል፤ ለተፈፃሚነታቸውም ተዛማች የሆነ የገንዘብ ምንጭ መገኘቱንና ለታለመለት አላማ መሰራጨቱን ያረጋግጣል፤

፰. በሬዚሊየንስ አግባብ ፍላጐት መርና ችግር ፈቺ የሆነ ጥናት ተፅዕኖ ዳሰሳ ከዩኒቨርሲቲ፣ ከምርምር ማዕከላትና ከሌሎች ትምህርታዊ አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፤»

፪. የደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፮)፣ (፯) እና (፰) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፱)፣ (፲) እና (፲፩) ሆነዋል፡፡

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Regulation"** mean the Addis Ababa City Government Strategic Programs Management Office Regulation No. 147/2023;
2. The words and phrases defined in the regulation shall also be applied in this regulation.

**3. <u>Amendment</u>**

Regulation No. 147/2023 that was issued for the Establishment of the Addis Ababa City Government Strategic Programs Management office is hereby amended as follows.

1. The following new sub-Article (6), (7) and (8) is added following sub-Article (7) of Article 5 of the regulation:

   "6. establish partnership with various local, regional and foreign private sector bodies for the implementation of the resilient strategy;

   7. prepare profitable projects for the implementation of the resilience strategy for all sectors; make sure that financial resources are obtained for its practicality and such is allocated for the intended purpose;

   8. conduct resilience based demand driven and problem solving studies and impact assessments in collaboration with universities, research centers and other educational institutions.

2. Sub-Article (6), (7) and (8) of Article 7 of the regulation has become sub-Article (9), (10) and (11) in their order respectively;

፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

4. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force as of this Jun 28th, 2024.

**Done at Addis Ababa, this Jun 28th, 2024**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**